## የሁለት ሺህ ዓመቱ በዓል የኢትዮጵያችንን መሠረታዊነት ያረጋግጣል!!

ከ ዘነበ በቀለ

ዘመን ተለውጦ ዘመን ሲተካ ፍጥረታት ሁሉ ለውጥን ያበስራሉ። ዕፅዋት ያሸበርቃሉ። አዕዋፋት ይዘምራሉ። የሰው ልጆችም የዚህን ለውጥ በተስፋ በመጠበቅ በህይወታቸው ላይ የሚያመጣውን በጎ ሁኔታ ሁሉ የመመኘትና መጭውን ዘመን በክብር የመቀበል ልምዶች አሏቸው። ሀገራችን ኢትዮጵያ የዚህ አይነቱን ፀጋ የተላበሰች ሀገር በመሆኗ የዘመን ለውጥን የምትቀበለው በነጫጭ የባህል ልብሶቿ በዐደይ አበባው፤ በእንግጫው፤ በቄጠማው፤ በጠጅሣሩ ሁሉ በመታገዝ ነው። እኛም ልጆቿ የዚህ ሁሉ ባህላዊ እሴቶች ተገዥ በመሆናችን ባህላችንን እንወደዋለን፤ እናከብረዋለን። በችቦው እንደሰታለን። በመዝሙሩ እንረካለን። እንኳን አደረሰህ፤ እንኳን አደረሰሽ! መባባሉ ውስጣዊ ደስታ ይሰጠናል። ይህን መሳዩን ወርቅ ባህል ያቆየችንን ውድ ሀገራችንን ከልብ እንወዳታለን። ያለፉትንም አባቶቻችንን እና እናቶቻችንን እናፈቅራቸዋለን፤ እናከብራቸዋለን። ምንም አይነት መከራ፤ ምንም አይነት የተዝናና ህይወት ቢገጥመን ይህንን ስሜታችንን ሊለውጠው አልቻለም። ስለዚህም በሄድንበት ስፍራ ሁሉ ስሜቱንና ፍቅሩን ይዘነው እንዞራለን።

ለዘላቂው ህይወት በጎ ምኞትን ሰንቆ የያዘው ተስፋችን የጀመርነውን ለመቀጠል፤ ያሰብነውን በተግባር ለማዋል፤ የወጠነውን ለማጠናቀቅ፤ ስለሚያስችለን አዲስ አመትን የምናከብረው በሙሉ ልባዊ ስሜት ነው። በተለይማ ያሁኑ አይነት በዓል በሺ አመት አንድ ጊዜ የሚገጥም በመሆኑ የተፈጥሮ ህግ ለፍጥረት ከሰጠችው መብቶች መሃል ከፍተኛው እንደሆነ ተደርጎ የሚታይ ነው። ሀገራችን ኢትዮጵያን በዐለም አደባባይ ያሳወቃት ትውልድ በዐድዋ ጦርነት ላይ ተፋልሞ ሲያልፍ የዛሬውን የ2ሺህ ዓመት በዓል ለማክበር የአንድ መቶ አሥራ አንድ ዓመታት ዕድሜ ያስፈልገው ነበር። ያ ሁሉ መስዋዕትነት የተከፈለው መጭው ትውልድ አንገቱን ቀና አድርጎ በታሪኩ ኮርቶ እንዲታይ ለማድረግ ነውና ያ! ትውልድ ዛሬም ከኛ ጋር ሆኖ በዓሉን በመንፈስ ያከብረዋል። ይሁን እንጂ! ለጋ ህይወቱን የቀጨበት የሀገር ጉዳይ ያ! አንገቱን ሳያቀረቅር ኮርቶ እንዲኖር ለማድረግ የተሰዋለት ህዝብ፤ አሁን ያለበት ደረጃ ላይ እንዳለ ሆኖ ቢመለከተው ሀዘኑ እንጂ ደስታው ጎልቶ እንደማይታይ ጥርጥር የለውም።

ታዲያ! እኛም 2ኛውን ሺህ ዓመት የምናከብረው በዚህ በተመሳቀለ ዘመን ውስጥ ሆነን በመሆኑ ለአውራሻችን ትውልድ ምስጋናችንን ስናቀርብ በራሳችን ትውልድ ለተጠናወተን የትውልድ ነቀርሳ ደግሞ ብሶታችንን፤ ቅሬታችንን፤ ሀዘናችንን፤ በመግለፅ ይሆናል። ይህን በዓል የምናከብረው ለዚህ ያደረሰንን አምላካችንን በማመስገንና የሀገራችንን ህዝብ ታሪክ በመዘከር የነፃነታችንን ገድል በማብሰር ይሆናል። እንጂ! ወያኔ/ኢህአድግ በሚፈልገው መልኩ የንግድ ዝርፊያ ለማጧጧፍ ከቶውንም አይደለም። ይህን በዓል የምናከብረው ዛሬ በየወህኒ ቤቱ

የሚሰቃዩትን የተመረጡ የህዝብ መሪዎችን በማመስገንና ገድላቸውንም አጉልቶ በማሰማት ይሆናል እንጂ! እንደ ወያኔ የፖለቲካ ትርፍ ለማግኘት በፍፁም ምኞት አይኖረንም። ሚሊየኔሙም ባላሳየው በጎ ገፅታ የሀሰት ካባ አልብሰን ለማሽቀርቀር አንከጅልም።

ኢትዮጵያውያኖች ይህንን በዓል የምናከብረው፡

- በርካታ ወገኖቻችን በሀገራቸው ውስጥ የመኖር መብት ተነፍገው በየወህኒ ቤቶች የታጎሩበትን፤ የተሰወሩበትን፤
- በየመንገዱ የተጣሉበትን፤
- በኤድስ የሚያልቁበትን፤
- ዜጎች ከኖሩበት ስፍራ የሚፈናቀሉበትን፤
- በጎሣ፤ በጎጥ፤ በሃይማኖት ተለያይተው እንዲገዳደሉ የተደረጉበትን፤
- ወገኖቻችን በዐረብ ሀገሮች ለባርነት የተሸጡበትን፤
- ህፃናት በለጋ ዕድሜያቸው ለበሽታ፤ ለልዩ ልዩ ልምዶች የተጋለጡበትን፤
- ወጣቶች ለባዕድ አገሮች አፍራሽ ባህል ተገዥ እንዲሆኑ የታጩበትን፤
- በአጠቃላይ ህዝባችን በወያኔ ጠባብ የጎጠኝነት ፖለቲካ ቀንበር ስር ወድቆ ላለፉት አስራ ስድስት ዓመታት የተሰቃየበትን ዘመን በአንድነትና በህብረት አስበነው ለመዋል ነው። አለበለዚያ! በምርጥ ወያኔዎች ጥጋብ የተራበው ደሃ ባልበላው እንዲያገሳ ምክንያት ለመሆን አምሮቱም ፍላጎቱም ሊኖረን አይችልም።

ይህንን በዓል የምናከብረው ውድ አባቶቻችንና እናቶቻችን ትተውልን ያለፉትን የነፃነት ዘመን ለዓለም ህዝብ ለማስተዋወቅ ነው። ይህንን በዓል ለማክበር ወያኔዎች የፖለቲካ ደጋፊዎቻቸውን የየሀገሮቹ መሪዎችና ሀብታም ነጋዴዎች ጋብዘው ድላቸውን ለማስመስከር ሲጥሩ፤ እኛ ደግሞ በችግራችን ላይ ከጎናችን ቆሞ ያስተናገደንን ተራ ህዝብ በየአለንበት ስፍራ ሁሉ ጋብዘን ለማመስገንና ለወደፊቱም እርዳታቸው እንዳይለየን ለማሳሰብ ነው።

ይህንን በዓል የምናከብረው አንዳንድ ወገኖቻችን ወያኔ በሚፈጥረው ታክቲክ ተዋዝተው የዚህን በዓል ታላቅነት በማሰብ ብቻ በተንኮል በተዘጋጀላቸው መረብ ውስጥ በመግባት በዚህ ዓይነቱ የማጭበርበሪያና የመበዝበዣ ክብረ በዓል ላይ ሀገር ቤት ድረስ ገብተው በሚሰጡት የገንዘብ ድጋፍ የወገናቸውን የኢትዮጵያን ህዝብ ሰቆቃ ለማረዘም ምክንያት እንዳይሆኑ ለማድረግ ነው።

ይህን በዓል ለማክበር ወያኔ የሞራል ብቃት የሌለው መሆኑን ስለምናውቅ አማራጭ ዕድል ለመስጠትም ጭምር ነው። በቀድሚያ የኢትዮጵያ ህዝብ ታሪክ መቶ አመት ብቻ ነው ብሎ ያለው ወያኔ በተንኮል ተነሳስቶ ለግል ኤኮኖሚው ማዳበሪያ ለማድረግ አስቦ ካልሆነ በስተቀር እንደምን አርጎ ሁለተኛውን ሺ. አመት የኢትዮጵያውያኖች በዓል ለማክበር ፈለገ? ይህ ለፖለቲካ ፍጆታው ያሰበው በዐል

በብዙ ሺህ የሚቆጠሩ ዜጎችን አስሮና ገድሎ በርካቶችን አደህይቶና ከሀገር አባርሮ፤ እነ አሉላ አባ ነጋ በደማቸው ያስከበሯትን አገር ያለባህር ወደብ አስቀርቶ፤ አንዱን ህዝብ ሁለት ቦታ ከፍሎ አጥር በማበጀት ነጣጥሎና በጠላትነት እንዲተያይ አድርጎ፤ በአጠቃላይ የኢትዮጵያን ህዝብ እርስ በእርስ አናቁሮ፤ ከሁሉም በላይ ደግሞ የዲሞክራሲ መብትን አፍኖ በመያዝ፤ ህዝብ የመረጣቸውን መሪዎች በፈጠራ ክስ በማንገላታት ላይ ባለበት ሁኔታ እንዲህ ዓይነቱን ህዝባዊ በዓል ለማክበር ማሰቡ ጤነኛ ፍላጎቱን ያሳያል ብለን ለመቀበል ወያኔም የመታመን ባህል የለው እኛም ለዚህ የሚያበቃ ሞኝነት አልተጠናወተንም።

በአንፃሩ ግን ይህ አማራጭ ክብረ በዓል ኢትዮጵያዊ ባለበት ስፍራ ሁሉ እንዲያከብረው ማድረጉ ከላይ ለተጠቀሱት ሁሉ ጥያቄዎቹ መልስ ያስገኛል። ስለዚህም 2ሺህ ዓመት በዓል ከወያኔ ግርግር በፀዳ መልኩ መከበር ያስፈልገዋል። ይህንን ሀቅ ከግንዛቤ ውስጥ በማስገባት በስደት በሰው አገር የሚገኙ ኢትዮጵያውያን ሰፊ ፕሮግራም በመያዝ የፖለቲካ ድርጅቶችና ማህበራዊ ስብስቦች እንዲሁም የሃይማኖት ተቋሞችን በጋራ በማሳተፍ ለማክበር ኮሚቴ እየመረጡና እየሰሩ በመሆናቸው ሊመሰገኑ ይገባል። ሌሎችም ተመሳሳይ እርምጃ በመውሰድና በሚፈጥሯቸው ኮሚቴዎች ኢትዮጵያውያንን በሙሉ በዝግጅቱ እያካተቱ እንዲንቀሳቀሱ መበረታታት አለበቻው።

በዚህም ኢትዮጵያውያን ወገኖች እጅ ለእጅ ተያይዘን ለመጓዝ የሚያስችለን የዕርቅ ዘመን እንዲሆንልን፡ የሰላምና የፍቅር ዘመን እንዲሆንልን፡ ወያኔ በክፍለ ዘመኑ በጎጥ ከፋፍሎ ሊበታትነን የተዘጋጀበትን መረብ በጣጥሰን ጥለን፤ በነፃነታችን ኮርተን፤ በአንድነታችን ፀንተን፤ ከድህነት የምንወጣበትን መንገድ ለመሻት፤ ለአንዲቷና መተኪያ ለሌላት ውድ ሀገራችን ኢትዮጵያ በጎነት ለመቆም በተባበረ ድምፅ ቃል ኪዳን የምንገባበት ዕለት ይሆናል። በመሆኑም 2ኛውን ሺ ዐመት በዓላችንን በዓለም ዙሪያ በስደት የምንገኝ ኢትዮጵያውያን የምናከብረው ይህን መሳዩን ራዕይ ሰንቀን ነው።

የኢትዮጵያ ልማትም ሆነ ሰላም ህዝቧን ባገለለ መልኩ ሊከናወን አለመቻሉን ማወቅ ብልህነት ይሆናል። ስለዚህም ለዚች ቅድስት አገር ኢትዮጵያ! ዘላቂ ህልውና ሕፃን፤ ልጅ፤ ዐዋቂ፤ አዛውንት ሳይባል ልጆቿ በሞላ ተገናኝተው ካለፈው ዘመን ትምህርትን ከመጭው ዘመን ተስፋን ሰንቀው መጓዝ ይኖርባቸዋል። ለዚህም ሁሉም የድርሻውን ያዋጣ!! ተረካቢው ትውልድ ሀገሩን በሰላም የሚኖርባት የሚማርበት የሚሰራባት ያደገችና የበለፀገች ሆና እንዲያት ያስፈልጋል። እንጂ! ታሪኳንና ነፃነቷን ያስነጠቀችና በውጭ ሀገር ሀብታሞች የተመረተ የአበባ ምርት የሚታይባት፤ የሀገሪቱ ዜጋ ለስደት፤ ለድህነት፤ ለበሽታና ለጉስቁልና ተዳርጎ የሚቀጥልባት ምድር ለማድረግ በታሰበ መልኩ 2ኛውን ሺ ዐመት ከወያኔ አመራር ጋር አናከብረውም።

ኢትዮጵያ በልጆቿ ህብረት ተከብራ ለዘለዐለም ትኖራለች!